# ዘ ሞስት ማግኒፊሺየንት ቲንግ (The Most Magnificent Thing)




## የአር አይ ኤፍ (RIF) መምሪያ ለወላጆች እና ለቤተሰቦች

**ይዘቶች (Themes)፣** ምናብ (Imagination)፣ ምህንድስና (Engineering)፣ ጽናት (Perseverance)

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፣** ይህ መጽሐፍ አንዲት ወጣት ልጅ እና የቅርብ ጓደኛዋ በጣም አስደናቂ ነገር ለመፍጠር ስትሞክር ያወሳል። ድንቅ ነገርን መፍጠር ማለት በሂደቱ ስህተት መስራት ማለት መሆኑን ለማወቅ የምታደርገውን ሂደት ይቀላቀሉ።

**ደራሲ እና ሰዓሊ (Illustrator)፣**
አሽሌይ ስፒረስ (Ashley Spires)



## የንባብ ጊዜ!

**ከማንበብዎ በፊት የግምት አስተያየትዎን ይስጡ (make inferences)፣** የሽፋን ሥዕሉን በመጠቀም ስለ ትንሿ ሴት ምን አስተያየት መስጠት ወይም መገመት ትችላላችሁ? ከውሻዋ ጋር ስላላት ግንኙነት ምን ማለት ትችላለህ? የታሪኩ መቼት ምን ይሆናል ብለህ ታስባለህ?

**በንባብ ወቅት፣ ግንኙነቶችን ይፍጠሩ (make connections)፣** ያልተሳካ ሃሳብ ኖሮህ የነበረበትን ጊዜ ታስታውሳለህ? ነገሮች ባንተ መንገድ ሳይሄዱ ሲቀሩ ተበሳጭተህ ታውቃለህ?

**ከንባብ በኋላ፣ ጥያቄዎች ይጠይቁ፣**

- ልጅቷን ድንቅ ነገር ለመስራት ያነሳሳት ምን ነበር?
- ልጅቷ ለፈጠራዎቿ የሚያስፈልጓትን ቁሳቁሶች ሁሉ ከየት ያገኘች ይመስልሃል?
- ውሻው ተስፋ እንዳትቆርጥ የረዳት እንዴት ነው?



## ተዛማጅ ተግባራት

**አስደናቂ ሙንቺ** (A MAGNIFICENT MUNCHIE)
ግብአቶች፣ ብስኩቶች (crackers)፣ የፕሪዝል እንጨቶች (pretzel sticks)፣ ዘቢብ (raisins)፣ የኦቾሎኒ ቅቤ (የክሬም ቺዝ ወይም ሌላ ወፈር ያለ ሊተካው ይችላል)

የእያንዳንዱን ግብዓት ግሮጾች አስቡ። ከነሱ ምን መፍጠር ይችላሉ? ሽረሪት? አበባ? ሰማይ ጠቀስ ፎቆች? ፈጠራዎን አንድ ላይ ለማያያዝ እንዲረዳዎ የኦቾሎኒ ቅቤን ይጠቀሙ። ንድፍዎን ሰርተው ሲጨርሱ ለትንሽ ጊዜ ያድንቁት-ከዚያም በብዛት!

**የአሳቢ ጊዜ!** (TIME TO TINKER!)
እንደገና ጥቅም ላይ ከሚውሉ እቃዎች የርስዎን የማሰቢያ ጣቢያ ይፍጠሩ። እንደ አስተያየት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፣ የካርቶን ቱቦዎች፣ የልብስ ስፒኖች (clothespins)፣ ቴፕ (tape)፣



ትንንሽ ሳጥኖች፣ ነትስ እና ብሎኖች (NUTS AND BOLTS)፣ የጎማ ባንዶች (RUBBER BANDS)፣ ክር ክር (STRING) የፕላስቲክ እቃዎች ወይም ማስመሪያ። አንዴ እቃዎቹን ከሰበሰቡ በኋላ፣ ምን መፍጠር እንደሚችሉ ያስቡ። መጀመሪያ ንድፍዎን ሊስሉ ይችላሉ ወይም ዝም ብለው እያሻሻሉ (TINKERING) ይሄዱ ይሆናል። ምን አይነት አስደናቂ ነገር ፈጠሩ? ድንቅ ስራዎን ይጥቀሱ!

**ሊሰሩት ይችላሉ** (CAN YOU DO IT)?
የሆነ ነገር መፍጠር ለመጀመር አንዳንድ ሃሳቦች ይፈልጋሉ? https://www.pbs.org/parents/ activity-finder/ ን ይጎብኙ እና ተግባሮች ይምረጡ።ጓደኞችዎን እና ቤተሰብ እንዲረዱዎት ይጠይቋቸው። ጥቂት ተግባራትን ከሰሩ በኋላ የራስዎን ፈጠራ ይሞክሩ!

## ተጨማሪ ሪሶርሶች (RESOURCES)



**በዚህ ደራሲ የተጻፉ ሌሎች መጻህፍት**

- **ኤዲየስ ኤንሰምብልስ** (2014 (Edie's Ensembles (2014))
- **ፔንግዊን ኤንድ ዘ ካፕኬክ** (2014) (Penguin and the Cupcake (2014)
- **ላርፍ** (2012) (Larf (2012))

©2025 Reading Is Fundamental, Inc.

Reading Is Fundamental
until every child reads